# በስምህ ልጠራ !

የልጅነት ወዳጅ፣ ጋሜ መቁረጫችን
ያርበኝነት ጥንስስ፣ ያመፅ ሙዳያችን
የዳገት የጫካ፣ የዱር ትውስታችን
በዱር በከተማ፣ ፋኖ አስተማሪያችን
የማሌው ደብተራው፣ ቅኔ ዘራፊያችን
በስምህ ልጠራ ልበል ትዝታችን

ተው ስማኝ ሀገሬ፣ ብለን ያዜምንበት
በቃላት ቱማታ፣ የተጫወትንበት
ከጁንታው፣ ከባንዳው፣ የተጣላንበት
ማሌ ድር አድርተን፣ ዲሞ ያቀለምንበት
በቁርና በርሀብ፣ የተፋተግንበት
ስምህ ከስማችን፣......
ደምህ ከደማችን፣ ቁርኝት አለበት

በስምህን ልጠራ፣.........

እንደ አባት፣ እንደ እናት፣ የተሸሸግንብህ
በስምህ ተጠርተን፣ ምለን ያደግንብህ
ለሊት በጨለማ፣ ዘብ የቆምን ለሥራህ
ቀትር ባአደባባይ፣ የታደን በስምህ
ከሰውና ካውሬ፣ የተናጠቅንብህ
ስምህ ታሪካችን፣ አርማችን ነው ስምህ

የወል ቤታችን ነህ፣ የኪዳን ህያው ቃል
ነበር የምንለው፣ የታሪክ መሰላል
የጽናት ትሩፋት፣ ተሻጋሪ ገድል
የመሠረት አለት፣ ትውፊት ያመጽ ግልገል
ኢትዮዽያዊ ወኔ፣ ያብዮት ክንድ ሾተል
በደም የጨቀየ፣ የተጋድሎ መድብል
የነጻነት ጠኔ፣ ያገር መውደድ ቁስል

EthioLion.Com

የትግል ጉልላት፣ የማእበል ደለል
እንዳምና ካቻምናው፣......
በስምህ ልጠለል፣ ዛሬም አለህ ልበል

በስምህ ልጠራ፣.........

በየቅጥሩ ደጃፍ፣ ስሙን ያስጠራችሁ
በዱር በሸለቆ፣ የተሰደዳችሁ
ግፉንም ችላችሁ በህይወት ያላችሁ
አካል ገብራችሁ፣......... . .
ቆስላችሁ ደምታች፣ ታሪክ የሰራችሁ
በጽናት ታግላችሁ፣...... . .
ወድቃችሁ፣ ቆማችሁ አርማ ያነሳችሁ
ኢ. ሕ. አ. ፓ ቢሏችሁ፣.........
ኢ. ሕ. . አ. ወ. ሊ ቢሏችሁ፣ ኢ. . ሕ. አ. ሠ ቢሏችሁ
ስሙ ነው ስማችሁ ገድሉም ታሪካችሁ
የመሰዋእት ልኬት ላገር መቆማችሁ
በድርጅት ፍቅር የመመነናችሁ

ዝናማ ነጭ ኩታ፣ በሂደት ይጎድፋል
ውበትና ለዛም፣ እንደዋዛ ያልፋል
ሎሚ ተራተራ፣ በዘመን ይሰምራል
እኛ ብቻ ደህና፣ ከርሞም ድል ያደርጓናል
ቀን የገበረለ እለት፣ ሃይ ዘራፍ ያሰኛል
ዘራፍ ማለት መልካም ለሁሉም ይበጃል
ትግሉ ከዳር ሳይዘልቅ ቀድሞ ድል ያውጃል
መሆንስ ካልቀረ ፋኖ መሆን ይሻል
አጠፋን ያሉ ለት ስር ሰዶ ያመሻል

በስምህን ልጠራ፣.........

አምባ ገነን ባንዶች ዛሬስ ምን ቀራቸው

EthioLion.Com

ለሀገር ፍቅር ስንል ተረገጥንላቸው
በጥይት ተቆልተን ጭዳ ሆንላቸው
ደማችን አፍሰሰን መንበር ገበርናቸው
ለስልጣን ጥማቸው ምንደኛ ሆንናቸው
ተዋርደን ተሰደን ጉልማ ቸርናቸው
በርሀብ ተጨማደን ጥሪት አስያዝናቸው

ዘመን ጉልላቷን ለግፈኞች ሰጥታ
የመከራ ምርጊት ወድቆ በእኛ ፈንታ
አንዴም ሰላም ሳናይ ሳናገኝ እፎይታ
ዓርባ ዓመት በቀንበር ኖረናት ሳንፈታ
እርሻው አረም ውጦት ምርት የለ ከጎታ
ዘሩም ተበትኗል ቀርቷል በየ ቦታ
ቃርሚውን ይሰብሰብ ይቅርብን ሁካታ

ማተቡ እማይላላ፣ ቢታሰር ቢፈታ
ከአላማው ጋር እሚኖር፣ ህልሙን ያበረታ
ፍጹም ሆኖ እሚዘልቅ፣ ሳይገብር ለቃታ
የሩቅ ምንገደኛ፣ የዛሬው አለኝታ
ደርሷል ወኽንዳችን፣ ለሀገር መከታ
የቁርጥ ቀን ልጅ ወግ፣ የማያመነታ

ከተማውን ዳስሶ፣ ገጠሩን አማክሎ
ዱር ገደሉን ጥሶ፣ ሸለቆውን ዘሎ
አለት ተንተርሶ፣ ካፊር ተመሳስሎ
የደም ላብ አፍስሶ፣ ካፊር ተቀላቅሎ
ዱር ለብሶ፣ ሳር መስሎ፣....... .
ሲረግጡት ስር ሰዶ፣ ሲነቅሉት ጎነቁሎ
ኢ.ሕ.አ.ፓ ሰርዶ ነው የማይጠፋ በቅሎ

አክሊሉ ህይሉ

(ፍራንክፈርት፣ ኦክቶበር - 20

EthioLion.Com